Ethiopiawinet Radio

Ethiopiawinet.net

## በደሴ ከተማ ምእመናንና ፖሊስ ተፋጠዋል፤ መካሪያ ሲተኮስ ወሎ አንድ ሙስሊም ሞተዋል

Tuesday, 30 June 2009 18:09

## ገዢው ፓርቲ ክርስቲያኑንና እስላሙን ማጋከሱን ገፍቶበታል

Ethiopia Zare (ማክሰኞ ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ .ም . June 30, 2009)፦ በደሴ ከተማ የቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን እንድትሰራበት ታቅዶበት የነበረው ቦታ ለረዥም ጊዜ ሲያወዛግብ ቆይቶ፥ የከተማው አስተዳደር ባለስልጣናት ቦታውን ሙስሊሞች ተቃውመውታል በሚል ስራው ተቋርጦ በድንኳን ሲቀደስበት ከቆየ በኋላ መንግስት መልሶ ቦታውን ለሌላ አገልግሎት ይዤዋለሁ በማለቱ፥ ዛሬ በደሴ ከተማ ብዛት ያለው ህዝብ የተሳተፈበት ሰላማዊ ሰልፍ እንደተካሄደና ከሰልፉ በኃላ በምእመናንና በፌደራል ፖሊሶች መካከል ረብሻ መነሳቱን የአይን ምስክሮች ገለጹ።

ነገሩ እንዲህ ነው። አዘዋ ገደል በሚባል ቦታ ላይ የቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን እንድትሰራ የአካባቢው ነዋሪዎችና ቤተክህነት በመወሰናቸው ቦታውን እንዲሰጣቸው ያመለክታሉ። በአካባቢው አዲስ የተገነባ መንደር በመኖሩ የቤተክርስቲያኗ ህንጻ እንዳይሰራ “የአካባቢው ሙስሊም ነዋሪዎች ተቃውመዋል” በማለት የአካባቢው ባለስልጣናት ቦታውን ይከለክላሉ። በመሀከሉም የሙስሊሙና ክርስቲያን ማህበረሰብ መሪዎች ሲነጋገሩ ሙስሊሞች ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳላቀረቡ እንዲያውም በቦታው መከከድ ሲሰራ ክርስቲያኑ ማህበረሰብ ተቃውሞ እንዳላሰማ ይነጋገራሉ።

ይሄንን የአስተዳደሩን ማጭበርበር ተከትሎ ምእመናን ተሰባስበው ወደ አስተዳደር ቢሮ በመሄድ በዛሬው እለት ቦታው እንዲፈቀድላቸው የጠየቁ ሲሆን ከአስተዳደሩ ምንም አይነት ምላሽ ባለማግኘታቸው በገደላገደል በተከበበችው ቦታ በመመለስ በተለይ ዲያቆናትና የአካባቢው ነዋሪዎች ጠወላ በማዘጋጀትና የህንጻ መሳሪያዎችን በማቀራረብ የህንጻ ስራው እንዲጀመር አደረጉ። አሰፍስፈው ይጠብቁ የነበሩት የፌደራል ፖሊሶች በቦታው በመድረስ በህዝቡ ላይ ተኩስ የጀመሩ ሲሆን በተነሳው ግርግር ምክንያት አንዲት ሙስሊም በገደል ወስጥ ወድቀው መሞታቸውን የአይን ምስክሮቹ ገልጸዋል። ይህ ዘገባ እስከተጠናከረበት ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን እየፈለጉና ተኩሱም እንዳልቆመ ለማወቅ ችለናል።

መንግስት በራሱ ምክንያት እምቢም እሺም ማለት ሲችል፥ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያላለውን ጠቅሶ የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች ለማጋጨት መሞከሩ፥ በቅርብ ጊዜ እየጨመረ የመጣ አዲስ የአገዛዝ ስልት ሲሆን አስተያየት ሰጪዎች ለዘመናት አበበና ከድጃ ሰይድና ለምለም ተጋብተው በሚኖሩባትና እስላምና ክርስቲያን ተከባብረው በሚያድጉባት ደሴ እንዲህ ያለውን ጸብ የሚያስነሳ ድርጊት

ሟደረጉ አሳዛኝና ህዝቡ በጥንቃቄና በአስተወሎት ሊከታተለው የሚገባ ነገር ነው ብለዋል። አስተያየት ሰጪዎቹ ጨምረውም ኢህአዴግ ያለፈውን ሀያ ዓመት በብሄረሰቦች ግጭት፤ ቀሪውን ሀያ ዓመት ደግሞ በሀይማኖት ግጭት ለመኖር ያሰበ ይመስላል ብለዋል።